# የመጨረሻው ሰይጣን

**ክፍል አራት**

**ካለፈው የቀጠለ**

**ከበልጀግ አሊ**

- እንደምን ከረሙ እማማ ?
- እንደምን ከርመኻል ልጄ?
- እንደው ጠፋሁ አደል ?
- ምን ይደርግ ብለህ የአገሩ ጠባይ አደል ።
- ልጅህስ ፣ ባለቤትህስ እንዴት ናቸው?
- ደህና ናቸው ። እኛ ጋ መጥተው ትንሽ ቀን እንዲቀመጡ ጠይቅልን ብለውኛል። እስቲን እሷን እጠይቃታለው ከፈቀደች አብረን እንሄዳለን። ልጄን ባለፈው ምን እንደነገሩዋት አላወቅሁም እንደው ስለኔ የልጅነት ታሪክ ለማወቅ እንቅልፍ አጥታለች።በጣም ነው መጠየቅ የጀመረችው ።
- ብዙም አላወራኋትም እንደው ትንሽ ስለአያትዋ ፣ ትንሽም ስለናንተም ነገርኋት። ልጄ ለመሆኑ ስለዚያ  ዘመን ትነግራታለህ?
- ብዙም ነግሬአት አላውቅም ።
- እሂማ ደግ አደለም!!!!

„ታዲያ ወጣቱ ከምን ይማር ብላችሁ ? አለበዚያማ ይህ አርቲ ቡርቲው የሚያወራውን እየሰማ የተሳሳተ አመለካከት ይዞ ነው የሚቀጠጥላችሁ። ታሪካችሁ እኮ ልትኮሩበት የሚገባ ነው ታላቅ ገድላችሁ ነው ። ድሎቻችሁ ተደብቀው ስላሉ አውጥታችሁ ማሳየትም አለባችሁ። ለምሳሌ መደራጀትን ያስተማራችሁ እኮ እናንተ ናችሁ ። ከእናንተ በፊት ባርቲ አናውቅ፤ኢ.አባ አደል የመጀመርያው ቀዳሚው ። ዴሞክራሲ አለገደብ የእናንተ ግኝት አደለም ብለህ ነው።ይኸው አለም ተመልሶ ሲጮህ የምንሰማው ዴሞክራሲ የሚለው ያኔ ከናንተ ነው ለመጀመርያ ጊዜ የሰማነው። ቆራጥነትስ ፣ለአላማ መሞትስ፣ የሰው ችግር መረዳትስ ፣ ስነስርዓትስ ልጄ። ያ ሁሉ ስው በሚስጥር ማደራጀት መቻል ፣ ስንቱን ልንገርህ “

አንተ ጋ ስመጣ ደግሞ ብዙውን እኔው እነግራታለሁ ። በልጅትዋ ላይ የአያትዋ ጠባይ እንዳለባት አውቄዋለሁ ። እንደመጣች ምን እንዳለችኝ ታውቃለህ ?“እዚህ ተቀምጠሽ ነው የዋልሽው ነይ እስቲ ትንሽ ወክ አድርገን እንምጣ “ ብላ ይዛኝ ወጣች ። የአባትዋ ተጋብቶባት የሰውን ችግር ማወቅ ብዬ አሰብኩ ።ተቀምጨ ውዬ እግሬ ተሳስሮ ነበር።

- ታስታውስ እንደሆን አላውቅም ። አንድ ወደ ዝሆን አምስት የሚኖር መልካም ድምፅ የነበረው ልጅ?
- ዞን አምስት ማለትዎ ነው ?
- አዎ ።

 ቀበሌውን በዝሆን ከፍለውት አልነበር። ታዲያ እርሱ በጣም መልካም ድምፅ ነበረውና ኢ.አባን መዝሙር ሲዘምር ልጆች ተሰብስበው  መስማት ይወዱ  ነበር። እኛም ታዲያ አንዳንዴ ግዜ ሲገኝ ጆሮአቸችንን መጣላችን መችም አልቀረም ነበር። ያኔ ታዳጊ ወጣት ነኝ ሲል ኩራቱ!!!! ።ታዲያ አንድ ቀን ከቀይ ሽብር በኋላ ቀበሌ ኪነት ሆኖ ተመርጦ ሲሰራ አገኘውና።

- አንተ ደግሞ እዚህ ምን ታደርጋለህ? ብለው የመለሰልኝና ፊቱ ምን ግዜየም ከፊቴ አይጠፋም ።ምን እንዳለኝ ታውቃለህ ?
- „የአቆሸሸከውን የአብዮቱን ሸማ እጠብ ተብዬ እሱን ለማንፃት እየታገልኩ ነኝ" አለኝ።
- ታዲያ ይሳካል'ኻል ወይ ?ብለው።
- „እሱ እንኳ በደም ተጨማልቆ ምኑን ይፀዳል ብለው እኔስ በአጥበው እነርሱ ወዲውኑ ያቆሸሹት የለም" አለኝ ።
- ታዲያ የአንተ ልፋት ለምኑ ነው? ብለው።
- „የድጋፍ ወረቀት እንዳይከለክሉኝ ብዬ ነው እንጂ እማማ"።
- የድጋፍ ወረቀት ለምን ያስፈልግሃል ?ብዬ ጠየቅሁት።
- እንደው ወደፊት ውጭ ሄጄ መማር እድል ካገኘሁ ብዬ ።ብሎ መለሰልኝ።
- ታገኛለህ ታዲያ ?ብለው።
- እየሳቀ „አዎ ከእነርሱ መጨረሻ ተመዝግቢያለሁ" ብሎ ካድሬውን ጠቆመኝ።
- እኔ እንዳላወቅሁ ሆንኩና እነርሱ እነማናቸው ? አልኩት
- እማማ ይህንን አጥተውት ነው። እንደው ከኔ ይውጣ ብለው ነው እንጂ።„እኛ ቀን ያጠብነውን ማታ ማታ የሚያቆሽሹት ማለቴ ነው" ብሎ ሳቀ አለ።
- በል እስቲ ይቅናህ፣ አሳብህን ያሳካልህ ፣እኔም በፆሎቴ አስብህሃለው ብለው ።
- እማማ እንዳያስቡ፣ እንዳይቸገሩ፣ ለጦላይ እንደው የድጋፍ ወረቀት አያስፈልግም አለኝ።
- ጦላይ ወጣቱን እያፈሱ ብሄራዊ ውትድርና የሚያሰለጥኑበት ቦታ መሆኑ ቢገባኝም፣ እኔም እንዳልገባኝ ምን ማለትህ ነው ? አልኩት።
- „ብሔራዊ ውትደርና ለመመዝገብ ማለቴ ነው። እዛ እነርሱ ስለሌሉ እኛ የመጀመርያ ነን ። መቸስ ዘመድ የለን ወይም ሃብት ማን ያድነናል ብለው። የውጭ ትምህርት እንደሆነ በፀረ አብዮት ያልተሳተፈ ነው የሚፈቀድለት።የአብዮቱን ነጭ ሸማ ያላቆሸሸ ማለቴ ነው ። ዩኒቨርሲቲ ልግባ ቢባል እዛም የድጋፍ ወረቀት ነው የሚጠየቀው። ለነገሩም አልሰሙም እንዴ በማትሪክ ውጤት እኮ ከርቸሌ ነው አንደኛ የወጣው ። ታዲያ ይህንን ሁሉ „አናርኮ" ውጭ ከሰደዱትማ ስንቱን ተምሮ መጥቶ አገሪቱን ሊቀይራት አደል ።እማማ ፡-

አብዮቱ ሞኝ አደለም ። አብዮተኞቹም ሞኞች አደሉም። መፈክሩ ለእያንዳንዱ እንደ ድጋፍ ወረቀቱ ነው።እንደችሎታው እና እንደፍላጎቱ የሚለው የሞኝ ፈሊጥ ነው የሆነው። እሱ ከኢሕአፓ ጋር ቀይ ሽብር ተፋፍሞበታል ። ባለፈው ሰሞን እስኮላርሺፕ ወጥቶ ነበር ታዲያ በጣም ያሳቀኝ በጦሩ ውስጥ ያለው ስልጣናቸው ለእስኮላርሽፑ ምደባ መጠቀማቸው ነው ።
የጀነራል ልጅ ምስራቅ ጀርመን ፣
የኮነሬል ቼክ ፣
የሻለቃ ልጅ ቡልጋርያ ፣
የሻንበል ኩባ ፣
የመቶአለቃ ልጅ እራሻ ፣
እኛ ደግሞ ወደ ጦሩ ግንባር በአስቸኳይ ነው የተመደብነው።

በካድሬው በኩል ከሄዱ ደግሞ ከምርት ካድሬው እስከ ኢሰፓአኮ አባለት ድረስ እንደ ድጋፍ ወረቀቱና የቀረነው ደግሞ ባስቸኳይ ወደ ጦር ግንባር በሚለው ህግ የወደፊት የህይወታችን እጣ ተመድባለች ። እኛን በቀይ ሽብር ብቻ መስሎን የጨረሱን በሁሉም ነውኮ ። እንዳንማር ከለከሉን ፣ እንዳንሰራ ከለከሉን ፣ አንመርጥ ፣ አንመረጥ ፣ ለነገሩስ ምርጫ ቢኖር አደለም ።

ለኢሰፓአኮ ምስርታ የወጣውን ህግ አላነበቡም። የኢሰፓአኮ አባል የሰደበ ፤ ለመስደብ ያሰበ ፤ የገላመጠ ፤ በህግ ይቀጣል ይላል ። አይ እማማ እኛ አለም ስትጨልምብን እነርሱ ውጭ ተምረው መጥተው እንደገና በቁማችን ሊገሉን ሳንወድ ተስማምተን እኛም ወደ ጦላይ እነርሱም ወደ ቦሌ ተለያየን ። እስቲ እንግዲ ማን ያውቃል ምን እንደሚመጣ ። ለአገራችን መሞታችን ባልከፋ ሲመለሱ ግን እኛን ገለው እነርሱ ላገራቸው እንደሞቱ ነው የሚሆኑት።ለመንግስተ ሰማያት የሚጠቅም የድጋፍ ወረቀት ይጠይቁበት ይሆናል ።

- ተመልከተው ልጄ የልጁን አነጋገር በቀይ ሽብር እራዕይ የነበራቸው ልጆች አጥተን እንደዚህ የተበላሸ ሰርአት አመጣን ። አሁንም ቢሆን ይህን የተደበቀ የኢአባ እራዕይ አውጥታችሁ ለወጣቱ ማስተማር ያስፈልጋል ። በአንዱ እሬሳ ላይ ጥቅሜን አስጠብቃለሁ የሚለው የኢሰፓ ውላጅ አስተሳሰብ ካልተወገደ አገር ተመልሳ አገር አትሆንም ።
- በል ብዬው ልሄድ ስል ተከትሎኝ መጥቶ እማማ ያኔ ያንን መዝሙር ያስተማረኝ እኮ እሱ ነው ብሎ የትልቁን ልጄን ስም ጠራ። አሁን ይህንን የማይረባ መዝሙር ዘምር ሲሉኝ አልቻልኩበትም አለኝ ።
- በርታ ካለዘመርክ ይገሉኻል ህጉን ታውቀዋለህ። ብዬው ተለያየንን ።

- አየህ ልጄ ያኔ የነበሩትን ልጆች ኢአባ በፍላጎታቸው ነው ያስተምራቸው የነበረው። ይህም እኮ አንዱ የተደበቀ ድል ነው ።ልጁ አየኸው ያለውን ለጦላይ የድጋፍ ወረቀት አያስፈልግምኮ ነው። በደርግ አብዮቱን መደገፍ አለብህ አሁን ደግሞ ዘርህን ነው የሚጠይቁህ ። ኢአባ የሚጠይቀው ግን ችሎታህን ነው።ስልጣን ላይ ብትወጡ ኖሮ ይህንኑ ነበር የምታደርጉት ብዬ አምናለሁ ። አሁን ደግሞ በውጭ አገር ያለውን ስመለከተው በድጋፍ ወረቀትና በኢሰፓ ኮታ የመጣው ስለሚበዛ ጫጫታውም እንዲሁ የበዛ ነው የሆነው ። ለአገራቸው የሞቱት ተረሱ፣ ተሰደቡ ፣ አሁን ደግሞ በዘር ሆኖ በንግድ ላይ የተመሰረተ ልዩነታችን እየጎላ መጣ ። የአሁኖቹ ይባስ ብለው ይህንን መሸጥ የለመደ የድጋፍ ወረቀት ሰልፈኛ፣ መሬት እያደሉ፣ መኪና በነፃ መሰገባት ትቸላለህ እያሉ፣ ኢንቨስተር ነህ እያሉ፣ በቀላል ገንዘብ ይገዙት ጀመር ። ታዲያ ይህ ብልህ ልጅ ብሄራዊ ውትድርና ሄዶ ሞተ፤ሌላም ምርጫ አልነበረውም። ለቅሶው ላይ ሄጄ ነበር። የሰፈሩ ሰው በጣም ስለሚወደው ብዙ ሰው ተገኘ። ሙሾም ተደረገ።

እንደው ባፍሩ ላይ

ዋይ ዋይ ወየው ወየው ዋይ ዋይ!! ወየው ወየው ዋይ ወየው ወየው!!

በተደመደመው

ወየው ወየው ዋይ ዋይ!! ወየው ወየው ዋይ ወየው ወየው!!

ሊሞሉበት ነው አፈር ሊሞሉበት ነው መረሬ
በአይኑ ከለላ በአይኑ ዳር ዳር

ዋይ ዋይ ወየው ወየው ዋይ ዋይ!! ወየው ወየው ዋይ ወየው ወየው!!

አቆርዳት ባረንቱ አፈቤት ተሰነይ
ናቅፋና ምፅዋ ይባላል ዋይ ዋይ
ወንድማማቾቹ አተው ገላጋይ።

የኤርትራ መሬት ደም የለመደው

የወንድሙን ስጋ ወንድሙ በላው
የኤርትራን እህል አልበላም እርሜ ነው
ያረሰው ዴሞፍተር ያበቀለው ደም ነው ።

ትልቁን ቀይ ሽብር ትንሹን ኤርትራ
አፈር ሳታለብሰው በላልህ አሞራ።

ሊሞሉበት ነው መረሬ ሊሞሉበት ነው አፈር
ዋይ ዋይ ወየው ወየው ዋይ ዋይ!! ወየው ወየው ዋይ ወየው ወየው!!

በዐይኑ ከለላ በዐይኑ ዳር ዳር።
ዋይ ዋይ ወየው ወየው ዋይ ዋይ!! ወየው ወየው ዋይ ወየው ወየው!!

ያኔ በቀይ ሽብር እዳር የነበርክ
በኤርትራው ጊዜ ማሀል ተገኘህ።

ሞት እኮ ፅዋ ነው ለሁሉም ይሰርሳል
እዳር የነበረው እማሀል ይውላል።

ያኔ በቀይ ሽበር መሃል ያየሁህ
ሀዘን ዕጣህ ሆኖ ዛሬም እዛው ነህ።

ሊሞሉበት ነው መረሬ ሊሞሉበት ነው አፈር
በዐይኑ ከለላ በዐይኑ ዳር ዳር።

ዋይ ዋይ ፣ወየው ወየው ዋይ ዋይ!! ወየው ወየው ዋይ ወየው ወየው!!

- ታዲያ ማታውኑ ለቅሶ ላይ ከእራት በኋላ ቆንጆትና አዳስ ስለልጁ አንስተው ስላለፈውም ግዜ ተንስቶ ስንጫወት አመሸን።ሃዳስ ታድያ እንደተለምደው ለቆንጆት ጀግና ፍለጋ ኤርትራ ድረስ ሂጄ የድሮ የሀገር ፍቅር ማህበር አባል አልፈልግልሽም ወደ ላይ ወጣ ብዬ ጀግና የወደቀበትን ቦታ ነው የማሳይሽ።ከፈለግሽም ቀዬን አፈር ላምጣልሽ ወይ ስትላት ሁላችንም ነገሩ ስለገባን በአንድነት ሳቅን ።
- እማማ እኔ አልገባኝም ምን ማለትዋ ነው ሃዳስ?
- የምትረሳው አይመስለኝም ያ ከናንተ ጋር እቤት የሚመጣው የአደይ ልጅ ። የቀዩዋ ትግሬ ልጅ ። እኝህ አማሴኑዋ ።

- አወቅሁት ሀይሌን አደለም የምትሉኝ።

- አዎን እሱን ማለቴ ነው ። እግዜር ነፍሱን ይባርካትና ። ገና እንደታሰረ ነው አሉ ስጋውን ይከትፉት ጀመር። ገረፉት ገረፉት ሰደቡት አንተ አጋሚዶ ሽፍታ አሉት ። እሱም

በትግል መሞት ህይወት ነው
ዳግም ትንሳዬ ልደት ነው ።

እያለ እየዘመረ ሲያስቸግራቸው ጊዜ አንተ ኤርትረዊ ነህ ኢትዮጵያዊ አደለህም ብለው አሉት። ታዲያ ያ ቆራጥ ኢአፓ እንደገና ባንዳ ማንነቴን አይነግረኝም ሲላቸው ግዜ ደማቸው ፈላና ጨንቀላቱን መትተውት ገደሉት ። አልወጣላቸው ቢላቸው እሬሳውን በሳንጃ ወጉት አውጥተውም እመንገድ ጣሉት ። ቅጥረኛ አሉት ። አረብ አሉት ፣ ሰደቡት ፣ አዋረዱት ፣ አስከሬኑ ላይ ወረቀት ፅፈው ለጠፉበት ። ኢአባ ኤርትረዊ ነው አሉን ። ምንም ሊፈቁት ያልቻሉት ግን በልጁ ውስጥ ተፅፎ የቀረውን የአገሩ ፍቀር በደሙ በሰፈራችን ላይ ፅፎ እንዳለፈው የሚገልፀው ታሪኩን ነው። እሂው ዛሬም በየለቅሶው ይነሳል።

ሃዳስ አንዳንድ ግዜ ለቅሶ ቤት ከቆንጆት ጋር ሲቀላለዱ ጀግና ማን እንደሆን ታውቂያለሽ አገር ፍቅር ድረስ አልሄድም የምትለው  እሱን በማስታወስ ነበር። እኛ እሱን ስታነስ ደስ እንደሚለን ስለምታውቅ በየጊዜው ታነሳዋለች። ቆንጅትም እሱን ስለምታውቅ ምንም መልስ የላትም ነበር ።ቆንጅትም መቀለድ ስላለባት ሃዳስ ሁልጊዜ ይህንን ለማስረዳት እጥረት ታደርጊያለሽ ትላታለች ። ሃዳስ ጥረትንና እጥረትን እንደማትለይ ስለምናውቅ ሁላችንም እንሰቃለን ።

ልጄ ይህም አንዱ ድላችሁ ነው ። ጓዶቻችሁ በዘር ሳይሆን በአላማ ተቃቅፈው ወደ መቃብር ወርደዋል ። አሁን ይህ አርቲ ቡርተው እንደሚያወራው ሳይሆን በእናንተ አካሃሄድ ቢሆን ኑሮ ይህ ሁሉ ፍጀት ባልደረሰ ነበር ። በጦርነት ደግሞ እሂው እንደምታየው ያመጣው ውጤት የከፋ ሆነ ። ይህንን ደግሞ ለወጣቱ ትውልድ ማስተማር ያስፈልጋል ።

- እንደው እማማ የሃዳስ እና የቆንጂት ነገር አስቤ አስቤ አልወጣ ቢለኝ ትንሽ ማስታወሻ ብዬ ይህንን ፃፍኩላቸው ላሰማዎት ?
- ምን ገዶኝ ታውቅ የል ፃፈው እያልኩ መጎትጎቴን።

ሀዳስ እና ቆንጅት በሰፈራችን ይኖሩ የነበሩ በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ፡፧ሀዳስ በወያኔ ከሀገር እንድትወጣ ሲደረግ የሰፈሩ ሰው የጠበቀው ስላልነበር በለቅሶ ነው የተሸኘችው ። ሀዳስና ቆንጅት እኔ የማስታውሳቸው በሰፈራችን ሰው ሲሞት በነበርው ሁኔታ ነው ። ቆንጅት የሴቶች እድር ሊቀመንበር ስትሆን ሀዳስ ደግሞ በእድሩ ከፍተኛ ተሰሚነት ያላት አባል ነበረች።

በሰለቅሶ ቤት ውስጥ እራት ከተበላ በሆላ የሁለቱን ቀልድ ለመስማት እዚያ የማያመሽ የሰፈሩ ሰው አልነበረም። ሀዳስ የቆንጅትን ሁኔታ እየቀዳች መቀለድ ስትወድ ቆንጀት ደግሞ የሃዳስን አማርኛ ስህተት በማውጣት አካባቢውን ያስደስቱ ነበር።

የቆንጅት ልጅ ማሙሽና የሃዳስ ልጅ አስመላሽ ሁለቱም ፧ አስመላሽ በሻብያ ማሙሽ ደግሞ በወያኔ፧ ስር ተሰልፈው በባድሜ ጦርንት  ከዚህ አለም አልፈዋል ። ይህ ግጥም ለእነርሱ ማስታወሻ የተፃፈ ነው።

ሀዳስ

አቤት ባድሜ አቤት ሽራሮ
የሬሳ ክምር ተከምሮ

ወንድም በወንድሙ ደም ሰክሮ
የቦንብ ወረዳ ደፍሮ
ዘሎ ገባ የዋሻውን በር ሰብሮ
ተናነቁ ጉሮሮ ለጉሮሮ።

አልወጡትም እዛው ቀሩ
በአንድ እንዳደጉ በአንድ ተቀበሩ
ምን ሆናችሁ እባካችሁ
እንዲህ ያጨካከናችሁ
ወይስ የላይ ፈሪ የታች ፈሪ አሉዋችሁ
እንደው በማታውቁት ነገር አለቃችሁ ።

ያኔ ድሮ እኛ ሰፈር
ስንጫወት በአፈር
ሀዳስ ኤርትራ ሳትሄድ ሳትባረር
ከሀዳስ ልጆች ከነክፍላይ
ጓደኞች ነበርን ከነአስመላሽ ከነሀይላይ።

ዘመቱ አሉ እነ ሀይላይ እነ አስመለሰሽ
ተገደው ነው ወይስ ሆነው የእናት ጡት ነካሽ
ሀዳስ ይህን ጉድ አየሽ!
አትቆጭም ነበር ተዉ አትሄዱም ብለሽ
ወይስ አንቺም ለራስሽ ፈራሽ
ተለጉመሻል አሉ አፍም የለሽ።

አንቺስ ብትሆኚ የኛይቱ!
ባትወልጂውስ አልነበርሽ እናቱ
እማማ እያለሽ አንቱ
አልነበረም ወይ ያደገው ከልፍኝሽ ከማጀቱ
የጎረቤት ልጅ የራስሽ ማለት ከንቱ ።

አትገላግይም ነበር ተው አይሆንም ብለሽ
ሊዘምት ሲነሳ ማሙሽ
ወይስ አንቺም እንደ ሀዳስ ለራስሽ ፈራሽ
ተለጎመ ወይ የአንቺም አፍሽ
ሀዳስ ከአንቺ
አንቺም ከሀዳስ አለተሻልሽ።

ምን አድርጊ ነው የሚሉኝ
ሆድ የሚያስብሱኝ
ልጄ ስንለው እማማዬ ሲለኝ
አልወለድሽኝም ቢለኝ ቢከዳኝ
መክረው ቢያራርቁኝ
ምርጫ ብለው ግራ ቢያጋቡኝ
ከነፃነት ከባርነት ምረጪ ቢሉኝ ።

ባርነት ነፃነት ማነው የዶለው ከመሀል
አልነበረም ወይ ምርጫው አንድነት ወይስ መገንጠል

ግራ አጋብተው አደናግረው ሲለያዩን
በግድ ተለያየን እንባ እየረጨን
ታዲያ ያም ለጄ ይህም ልጄ
እዬዬ ተረፈኝ
የወላድ አንጀት ያሳደገ እንቢ እያለኝ ።

ሀዳስ አስመላሽን ለኔ ትተሽ
ልጄን አደራ ብለሽ
ጡቴን እያጠባሁ እንዳይርበው
አዝዬ ነበር የማስተኛው
ጉዳይሽን ጨርሰሽ ስትመለሽ
ለናትነቴ ምን እነከን አገኘሽ
ልጅሽ አይደለም ሲሉኝ ምንው ዝም አሰኘሽ።

ያም ልጄ ይኸም ልጄ
ያሳደኩት በጄ
እስቲ ፍረጂኝ ወዳጄ።

በግድ ፈልቅቀው ለያዩን
አሁን ደግሞ በግድ አጋደሉን
ተይው ሀዳስ ቀን ይፍታቸው
ውስጣቸው እንደው አንድ ነው ።

ሀዳስ አንቺም እንደኔው
ተረፈሽ እንዴ እየዬው
ያም የወለድሽው ይህም ያሳደግሽው
አይደንቀኝም ቢተርፍሽ እየዬው።

ትዝ ይልሽል የኔ ልጅ ማሙሽ
አልወጣም ሲል ከጉያሽ
ከኔ ከእናቱ አንቺን ሲመርጥሽ
ብላ ስትይው አንቢ ሲልሽ
ስታጎርሺው እያባበልሽ
ምን ብሎ ይሆን ሆድሽ
ሲጋደሉ ልጆችሽ።

ሀዳስ

ስታለቅሽ አስመላሽ እያልሽ
ድቅን ሲልብሽ ማሙሽ
አለቀሽ አደል ልጆቼ እያልሽ
እኔም አልኩኝ እየዬ
አንዴ ማሙሽ አንዴ አስመላሽ ብዬ።

ለቅሶ ሆነ እጣችን
እያለቁ ልጆቻችን።

ያኔ ድሮ በሰፈሩ ሀዘን ሲሆን

ተጠራርትን ልንሄድ አብረን
ሀዘንተኞቹን እራት አብልተን
ገበታውንን አነሳስተን
ስንጨርስ ዕቃ አጥበን
እንጀምር ነበር ጨዋታችንን
የሰው ሃዘን ያረሳሳን እየመሰለን ።
ታዲያ ዛሬ የኛን ሀዘን
ማን ይድረሰን ጉዳችንን።

በይ እንግዲህ ደህና ሰንብች
ቻል አድርጊው ሀዘንሽን
ቻል አድርጊው ሀዘንሽን።

- ድንቅ አርገህ ተናገርከው ወስጄ ለአሮጊቶቹ ነው የማነበው።
- በሉ በሰላም ይክረሙ በሚቀጥለው ይገፎት ወደ እኛ ቤት እወስዶታለሁ ።

ስላም ክረም ልጄ ማምሻም እድሜ ናት ።
ስላም ይክረሙ እናቴ ስለኛ የሚያስብ ሁሉ ስላምን ያግኝ ።

ይቀጥላል።